

መንፈሳዊ ጽሑፍ

ልግስና ለተቸገሩት



Word from the Word
በ ዴሪክ ፕሪንስ

ዴሪክ ፕሪንስ ነኝ፤ ከቃሉ ለእናንተ የሚሆን መልዕክት ይዤላችሁ ቀርቤአለሁ።

> ቸር ሰው ይራራል ያበድራልም፥ በፍርድም ነገሩን ይፈጽማል። ለዘላለም አይናወጥም፤ የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል። ከክፉ ነገር አይፈራም፤ በእግዚአብሔር ለመታመን ልቡ የጸና ነው። በጠላቶቹ ላይ እስኪያይ ድረስ ልቡ ጽኑ ነው፥ አይፈራም። መዝሙር 112:5-7,9

መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ ስለ ልግስና መልካም ነገርን ይናገራል፤ ስለ ንፉግነት ግን የሚናገረው ምንም መልካም ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ የተሞላበትና አስተዋይ ልግስና ወደ በረከትና ብልጽግና የሚወስድ መንገድ መሆኑን ያስተምራል፤ ንፉግነት ግን ወደ ድህነት ያመራል።

መዝሙረኛው እዚህ ጋር ጻድቅ ሰውን ይስላል። እንዲህ ይላል፦ “ለዘላለም አይናወጥም፤ የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል።” ለምን? የዚያ ሰው ጽናት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? እርሱ ቸር ነው፣ በልግስና ያበድራል፣ ስጦታዎቹንም በውጪ ለድሆች በትኗል። ስለዚህ ዘማሪው፣ “ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል” ይላል። ዛሬ ብዙዎቻችን ለድሆችና ለተቸገሩ ሰዎች ያለን አመለካከት ለጽድቃችን ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ማስታወስ ያለብን ይመስለኛል። እግዚአብሔር የድሆችን ጩኸትና ፍላጎት ችላ ስለሚሉ ሰዎች የሚናገረው ምንም መልካም ነገር የለም። ይህ ጽድቃችንን ለማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን እናስታውስ።

© 1970 - ዴሪክ ፕሪንስ ሚኒስትሪዎች ኢትዮጵያ

መንፈሳዊ ጽሑፍ ★

ግልባጭ: WD-WFTW-087-AMH

መጨረሻ የዘመነው: 28 Oct 2026

ድህረገፅ: Derekprince.com/am/resources

